እስከ ዛሬ «ጓድ» ናቸው!
በኢትዮጵያ ብሔራዊነት ላይ ፀሀይ አጥልቀው፤
በልጆቿ ደም ታጥበው፤
በአፅማቸው ሰባሪ፤
በስብዕናቸው ምጸት፤
በስቃያቸው ላይ አብዮታዊ እርምጃ የተራመዱ፤
አምባገነንነት ግነት፤
የሞት ጽልመት መጋረጃ፤
ኢትዮጵያ ሕልም ላይ የጋረዱ፤
የኢሠፓአኮ፤ የኢሠፓ፤ ገለመሌ፤
ማዕከላዊ ኮሚቴ፤
የሥልጣን ድሪቶ፤ ቡትቱ.....!
እንዳጠለቁ ናቸው ጭምብል፤
የሚሹ ሊቀዳጁ የአብዮት ድል።
እጆቻቸው ቀይ ናቸው፤
በንጹሀን ደም የበለዙ፤
ፍትሕ ሸሽተው! ሀገር ወደው ይሆን? የ-ተ-ጋ-ዙ?!
ይኖራሉ ዛሬም፤
በሽፍጠኛው ዓለም፤
ተንደላቀው፤
የኢትዮጵያ ልጆች መቃብር ላይ ቆመው፤
ይደነፋሉ!!!
«ጓድ» ነን «ጓዶች» ነን እያሉ!
ምን ቸገራቸው?
የልብ ሕመም ጸጸት፤
መቅኔ አድራቂ ምጠት፤
የሚያወጣ ከሰውነት፤
መሪር ዕንባ አልወረዳቸው፤
ወዮ! ያላሉለት ሀዘን አልነካቸው፤
እነሱ የአብዮት ልጆች «ጓድ» ናቸው።
የዚያች ሀገር የመከራ መርግ ያልተጫናቸው።
«ጓዶች» በሙሉ ውጪ ናቸው፤
ከነ-እንቦቀቅላ ልጆቻቸው!።
እርያማዊውን ፍርድ በትእግስት፤
ለሚጠብቀው ለዚያ ሕዝብ፤
እንባ ሰቆቃ ለሆነው ምግብ፤
ችግር ሰደት የዕለት ቀለብ፤
ከድጡ ወደ-ማ-ጡ!
ከእሳቱ ወደየሚፋጀው ረመጡ!!!
ለተገፋው —፣
ከቀን ወደማታው፤

ከማታው ወደቀኑ ጅብ–መንጋጋ ለተጣለው፤
ያጣው ሊታደገው፤
ፍትሕ ለተነፈገው፤
ይብላኝለት ለዚያ ሕዝብ እንጂ፤
እነሱማ ምን ቸገራቸው?
መሪዎች ናቸው የአብዮታቸው!!!
ካድሬ የትግላቸው፤
ገዳይ ለ–ሀ–ገ–ራ–ቸ–ው።
አሁንም ቢቻል፤
ዕድሉ ቢገኝ፤ በወልም ይሁን በግል፤
ዛሬም ይምላሉ ይገዘታሉ፤
ለአብዮት ሲሉ ገድለው፤ ገድለው ሊጥሉ፤
ለምን ብትሉ?
«ጓድ» ናቸዋ! የኮሩ በትግላቸው፤
ሰደድ ናቸው ነበልባል፤
በአዋጅ የረሸኑ፤
በፀረ-አብዮተኛ ላይ ያለፍርድ የበየኑ፤
በሀገር ወዳድነት ስም ሀገር የሸጡ፤
በየአቅጣጫው የፈረጠጡ፤
አብዮት ቢፈነዳ ለሥልጣን ሽሚያ የሚመጡ፤
ደግመው «ጓድ» የ–ሚ–ባ–ባ–ሉ!
በይፋ የሚገድሉ፤
ፈረንጅ ሀገር ፈረንጅ ሆነው፤
ከፍትሕ ወላፈን ተደብቀው፤
የአብዮታዊነት ስሜት የሚተናነቃቸው፤
አሁንም እኮ «ጓድ» ናቸው፤
የህዝብ ቁጣ ሞገዳዊ፤
እስኪመጣ፤
አምላከ ኢትዮጵያ፤
አምላከ ንጹሀን እስኪፈርድባቸው።

ሀረገወይን ስለሺ፤
የካቲት-፳፻፬ ዓ.ም